# መጽሐፈ ሩት (14)

## ጥናት አንድ (ሩት 1:1-5)

የጥናት ዓላማ: በውሳኔአችን ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔርን ካላስገባነው በመጨረሻው የምንከፍለው ዋጋ እንደሚኖር ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን በምድሪቱ ላይ ረሀብ ሆነ...» ሩት 1:1

1. በቁጥር 1-5 ባለው ክፍል ውስጥ የሰፈረውን ሀሳብ በራስህ ቋንቋ ተናገረው::
2. ዘዳ 11:16-17 ትን በማንበብ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእስራኤልን ህዝብ በተመለከተ ረሀብ ምን ይጠቁማል?
3. «መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን በምድሪቱ ላይ ረሀብ ሆነ...» ረሀቡ በዚህ ዘመን ውስጥ መከሰቱን በማስፈር ጸሐፊው አተኩረን ልንመለከተው የፈለገው ነገር አለወይ? ካለስ ምንድነው ትላለህ?
4. አቢሜሌክ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ሞአብ ለመግባት የወሰነበት ምክንያት ምን ነበረ?
5. በቁ 1 መሰረት አቢሜሌክ በሞአብ ለመቆየት ያሰበው ለምን ያህል ጊዜ ነበረ? እሱ ያሰበውንና የቆየበትን ዘመን ስትመለከት ልዩነት ታያለህ ወይ? ከሆነስ ከዚህ ምን ትማራለህ?
6. እነዚህ ቤተሰቦች ወደ ሞአብ ለመሄድ ሲነሱ የጠበቁት ምን ነበር? በጠበቁትና በገጠማቸው ሁኔታ መሀል የምታየውን ልዩነት አስረዳ::
7. አቢሜሌክ ረሃብን ብቻ ምክንያት አድርጎ ወደ ሞአብ መጓዙ ትክክል ይመስለሃል ወይ? ካልሆነስ ሌሎች ምን ተጨማሪ ነገሮችን ማየትና መመዘን ነበረበት ትላለህ?
8. ውሳኔን በተመለከተ አማኝ ከዚህ ቤተሰብ ሊቀስም የሚገባው ትምህርት ምንድንው?
9. ጌታ በዚህ ትምህርት ውስጥ ለግልህ የተናገረህ እውነት ካለ ለወገኖች አካፍል::

# ጥናት ሁለት (ሩት 1:6-21)

የጥናት ዓላማ: እግዚአብሔር አምላካችን የቃልኪዳን አምላክ ስለሆነ እኛም የምንገባው ማናቸውም ቃልኪዳን ለመጠበቅ የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ እንደሚጠበቅብን ለመማር:: የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ከዚያም ዖርፋ አማቷን ስማ ተሰናበተቻት ሩት ግን ልትለያት ስላልፈለገች ተጠመጠመችባት::» ሩት 1:14

1. የተነበበውን ምንባብ በራስህ ቋንቋ ቅደም ተከተሉን ጠብቀህ ታሪኩን ተናገር::
2. በምንባቡ ውስጥ የእስራኤል ህዝብ እንጀራ እንዳገኘ እናነባለን:: ሰለ እንጀራው ምንጭ ክፍሉ ምን ይነግረናል? ይህ እውነት በእኛ ስጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ህይወት ሊኖረው ስለሚገባው ሥፍራ ሃሳብ ስጥ::
3. ኑሃሚን ለሩት የሰጠቻት ምክር ጥበብ ያለበት ሆኖ ይታይሃል ወይ? ካልሆነስ ምን ብትመክራት የተሻለ ነበር ትላለህ?
4. በቁጥር 10 ና 14 ላይ ሩትም ሆነ ኦርፋ ሁለቱም ውሳኔ እንደወሰኑ እናነባለን:: በውሳኔዎቻቸው መካከል ልዩነት ታያለህ ወይ? ከሆነ ልዩነቱ ምን ነበረ::
5. በቁጥር 11-13 ውስጥ ኑሃሚን ምራቷን ለማሳመኛ የተጠቀመችባቸውን ሀሳቦች በሙሉ ዘርዝር:: ኑሃሚን በጊዜው ስለራሷ ስለነበራት አመለካከት ንግግሯ የሚያስረዳን ነገር ምንድነው? በዚህ ሁኔታ ለመሆኗ ተጠያቂ ማንነው?
6. ስለአቢሜሌክ ቤተሰብ መንፈሳዊ ህይወት በአጠቃላይ ገምግም ብትባል የምትሰጠው አስተያየት ምን ይሆናል? መልስህን በቃሉ በመደገፍ ለመናገር ሞክር::
7. የኑሃሚንንና የምራቷን ግንኙነት በመመልከት ስለአማችና ስለምራት በብዙዎች ውስጥ ያለውን ስር የሰደደ አመለካከት የሚቃረንበትን መንገድ ተናገር::
8. ሩት የወሰነችውን ውሳኔ ጠልቀን ስንመረምረው ከባድ ውሳኔ መሆኑን እንረዳለን:: ውሳኔውን ከባድ ከሚያደርጉት ነገሮች መሃል ጥቂቶቹን ዘርዝር::
9. አንተስ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው (ለቤተ ክርስትያን: ለወዳጅህ: ለትዳር ጓደኛህ ወዘተ) የገባነው ቃል የሚያስከፍለህ መሆኑ ሲገባህ (ሲነገርህ) መውጫ መንገድ ታብጃለህ ወይስ በቃልህ በመቆም ትጸናለህ?

# ጥናት ሶስት (ሩት 1:22-2:7)

የጥናት ዓላማ፡ በረከትን ከእግዚአብሄር የሚመጣ እንደሆነ በማመን የተዘጋጀልንን በረከት ለመቀበል ደግሞ በስራችን ታታሪዎች ሆነን መገኘት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «...ወደ አዝመራው ቦታ ገብታ ከጠዋት አንስቶ እስከ አሁን ያለማቋረጥ ስትቃርም ቆይታለች፡፡» ሩት 2:7

1. በዚህ ምንባብ ውስጥ የተካሄደውን ድራማ መሰል ታሪክ በራስህ ቋንቋ ተናገረው፡፡
2. ሩት 1:1 ንና ሩት 1:22 ትን ጎን ለጎን ስታነብ ምን ታስተውላለህ? መልስህን አስረዳ፡፡
3. 2:1-3 ሰናይ እግዚአብሄር ለሩት ቦዔዝን እንዳዘጋጀላት እናነባለን፡፡ በዚህ ወስጥ የሩት ድረሻ ምን እንደ ነበረ ተናገር፡፡ ከዚህ ለራስህ ምን ትማራለህ?
4. በዚህ ክፍል ስናነብ ሩት ወደስራ ስትሰማራ እንመለከታለን፡፡ ከኑሃሚንና ከሩት ማንኛቸው አስቀድሞ ለስራ መውጣት እንደነበረበት ትላለህ? ለምን ይህንን ለማለት ቻልክ?
5. በ2:4 ላይ በሚታየው በቦኤዝና በሰራተኞቹ መካከል በሚደረገው የሰላምታ ልውውጥ ውሰጥ ጎልቶ የሚታይህን ነገር ተናገር፡፡ የሰላምታው አይነት በተለይም መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን መሆኑ ልዩ ትኩረት የሚያሰጠው ለምንድነው?
6. ከላይ የተመለከትነው የሰላምታ ልውውጥ ስለ ቦዔዝ ምንነትና ማንነት ሊጠቁመን የሚችለው እውነት ምንድነው?
7. ዘሌ 19:9-10 እና ዘዳ 24:19-21 ትን በማንበብ በቃርሚያ ስራ የሚሰለፈው ምን ዓይነት ሰው ነው? ሩት በዚህ ዓይነቱ የስራ መስክ ላይ ለመሰለፍ መፍቀዷ ስለ እርሷ ባህርይ ምን ይነግረናል?
8. ሩት 2:4 ላይ ቁ 5-7 የአጫጆቹ አለቃ ስለ ሩት ለአለቃው የሰጠውን መልስ ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩበት፡፡ የሩትን ባህርይ በተመለከተ ከክፍሉ ምን ትማራለህ?
9. ከሩት ህይወት እግዚአብሄር ያስተማረህን ነገር ለወገኖች አካፍል፡፡

# <u>ጥናት አራት (ሩት 2:8-23)</u>

የጥናት ዓላማ: በአስቸጋሪ ሁኔታታውስጥ የሚገኙትን ክርስትያን ወገኖች በትንሽ ነገር ልናበረታታቸውና መንፈሳቸውን ልንቀሰቅስ እንደምንችል ለመማርና ለዚህ በጎ ስራ እርስ በእርስ ለመበረታታት::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ከሴት ሰራተኞችህ እንደ አንዷቱ መቆጠር የማይገባኝ ብሆንም እንድጽናና አድርገሽኛል...» ሩት 2:13

1. ቦዔዝ ሩት ለተሰማራችበት የቃርሚያ ስራ ለማበረታታት በ2:8-9 ላይ የሚናገራቸውን ቃላት ዘርዝር::
2. እነዚህ ቦዔዝ የተናገራቸው ቃላት በሩት ህይወት ውስጥ ያመጣው ለውጥ አለ ብለህ ታምናለህ ወይ? መልስህን አስረዳ::
3. ቁጥር 8 ና 22 ከቦኤዝ ወደ ሌላ እርሻ እንደማይኖርባት የተነገራት ሃሳብ አንተ ከተቤዠህ ከኢየሱስ ጋራ ሊኖረህ ስለሚገባህ ግንኙነት ምን ያስተምርሃል?
4. በቁጥር 10 ላይ ሩት የሚቤዣት ሰው ላሳያት ቸርነት የሰጠችው ምላሽ ምን ነበረ?
5. በዚህ ስፍራ ማለትም በሩት 2:8-10 በቦዔዝና በሩት መካከል ሲካሄድ የምናየው የሃሳብ ልውውጥ በእኛና በጌታ መሃል ከተካሄደው ታሪክ ጋራ የሚመሳሰልበትን መንገድ በማነፃፀር አስረዳ::
6. በቁጥር 11-12 ውስጥ ቦዔዝ ለሩት እንደገና የሚናገራት ነገር ምንድነው? ለዚህ ንግግሩ ደግሞ የሩት ምላሽ ምን ነበረ?
7. ቦዔዝ ስለዚች ሴት ማንነት (መበለት፣ ደሀ፣ ሞዓባዊ...) መሆኗን ጠንቅቆ እያወቀ እንደተቀበላት ከቁ 11-12 እንመለከታለን:: ይህ ታሪክ ከአንተ ህይወት ጋራ እንዴት ሊገናዘብ እንደሚችል ተናገር::
8. በ2:11-12 ቦዔዝ ለሁለተኛ ጊዜ የተናገረው ንግግር በሩት ህይወት ውስጥ ስላፈራው ፍሬ ሩት ከተናገረችው ንግግር መሀል ቢያንስ ሁለቱን ጥቀስ::
9. ከአንደበትህ የሚወጡትን ቃላት ሰዎችን ለማበረታታትና ለመፈወስ ምንያህል ትጠቀምባቸዋለህ? አንደበትን ለበረከትም ሆን ለመርገም መጠቀም ስለሚቻል በማስተዋል መጠቀሙ የእያንዳንዳችን ሃላፊነት ይሆናል::

# ጥናት አምስት (ሩት 3:1-18)

የጥናት ዓላማ: ጌታ ቃሉን ለመጠበቅ የሚተጋ አመላክ እንደሆን አምነን በቃሉ ላይ በማረፍ በትዕግስት ልንጠብቀው እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ልጄ ሆይ፣ የሚሆነውን ነገር እስክታውቂ ድረስ ታገሺ፣ ጉዳዩ ዛሬውኑ እልባት ካላገኘ ሰውየው አያርፍም» አለቻት። ሩት 3:18

1. በ3:1 ላይ ኑሃሚን እረፍት አልፈልግልሽምን ስትል ምን ማለቷ ነው? በ1:9 ላይ ከተመኘችላቸው እረፍትስ በምን ይለያል?
2. 3:4, 8, 14 ላይ ሩት የምትፈልገውን ከቦኤዝ ለማግኘት ትህትና ጠይቋታል። ይህ ድርጊት ሌሎች ወደ ጌታታመምጣት ለሚፈልጉስ እንዴት ይሰራል?
3. ሩት የተቀበለችውን ምክር ሁሉ አንድም ሳታስቀር በሥራ ላይ ማዋል ምን ያህል ከብዶ ታየዋለህ? ከተቀበለችው ምክሮች ሁሉ በተለይ የትኛው ከብዶ ይታይሃል?
4. ቁ 10 ላይ «ከዚህ በፊት ካደረግሽው ይልቅ ያሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል።» ሲል ስለ የትኛው በጎነት ነው የሚናገረው?
5. ቦኤዝ በቁ 12 ላይ «ከእኔ ይልቅ መቤዥት የሚገባው የቅርብ የስጋ ዘመድ አለ» ሲል አለመፈለጉን ያሳየናል ወይ? ካልሆነስ ይህ አባባል ምን ያመለክተናል?
6. ሩት ወደ ቦዔዝ በመጣች ቁጥር ከራሷ ያለፈ ነገር አግኝታታእንደምትመለስ ደጋግመን ተመልክተናል። ይህ እውነት አንተ ከጌታህ ጋራ ሊኖርህ ስለሚገባህ ግንኙነት ምን ያስተምርሃል?
7. ቁጥር 17-18 ትን በማንበብ ሩት ለቦኤዝ የመቤዥት ጥያቄዋን ካቀረበች በኋላ ማድረግ የነበረባት ነገር ምን ነበረ? እንድትታገስ ለሩት የተሰጣት ምክንያትስ ምንድነው?
8. ቁጥር 17-18 በሰፈረው መሰረት ሩትን በሚቤዥው ሰውና እኛን በተቤዥን ጌታ መካከል የሚታየው የባህርይ ተመሳሳይነት ምን እንደሆነ ተናገር።
9. ለሩት የተሰጣት ምክር ለኛስ ምን ያህል አስፈላጊ ሆኖ ታየዋለህ? ለምን?

# ጥናት ሰድስት (ሩት 4:1-12)

የጥናት ዓላማ፡ ሕግ ሊቀበለን ያልፈለገንን እኛን በፍቅሩ የተቤዠንን ጌታ ኢየሱስ ለማመስገን እንደገና እንድንነቃቃ ለማድረግ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «...አንተም በኤፍራታ የበረታህ ሁን፤ ስምህም በቤተልሔም የተጠራ ይሁን።» ሩት 4:11

1. በከተማይቱ በር አደባባይ ላይ በቦኤዝና በሌላው የቅርብ ዘመድ መሃል እየተካሄደ ያለውን ውይይት በራስህ አማርኛ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ተናገር።
2. የሚቤዥ ሰው ማሟላት የሚኖርበት ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ወይም መስፈርቶች አሉ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው?
3. እኛን የተቤዠን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ሶስት መስፈርቶች ያሟላል የምትልባቸውን መንገዶች ተናገር፡
4. ለመቤዠት የቀረበው ሌላኛው ሰው እንድቤዥ ሲጠየቅ መልሱ ምን ነበረ? በኋላ መልሱን ያስቀየረው ነገርስ ምንድነው?
5. ይህንን የቅርብ ዘመድ ከቦኤዝ ጋራ ስታነፃፅረው ምን ልዩነቶች ትመለከታለህ?
6. በዚህ ስፍራ ሩትን ለመቀበል እንቢ ያለው ሰው ሕግን እንደሚወክል ይመስላል። ሕግ ደግሞ እኛን እንደ ሩት ላለመቀበል እንቢ ያለበትን መንገድ አስረዳ።
7. ቁ 10 ላይ «...እኔ ልቤዠው አልችልም» ይህ ሰው ሕግን እንደሚወክል አድርገህ ውሰድና ይህ አነጋገሩ ከገላትያ 3:21 ጋራ በሃሳብ የሚመሳሰልበትን መንገድ አስረዳ።
8. በቁጥር 10 ላይ ቦኤዝ ለሌሎች የሚኖር ሰው እንደሆነ የሚጠቁመን ዋነኛ ሃሳብ የትኛው ነው?
9. ቦኤዝ ከሽማግሌዎቹና በከተማይቱ በር አደባባይ ከነበሩት ሁሉ ምስጋናን እንደተቀበለ ቁ 11 ላይ እናነባለን። እኛን በደሙ ለተቤዠን ሊሰጠው ስለሚገባው ነገር ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
10. ሕግን በተመለከተ ማናችንም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳልነበረን ኤፌሶን 2:11-13 በግልፅ ያሳየናል። ማንነትህን/ሽን እያወቀ የተቀበለህን/ሽን ጌታ ለማመስገን በፊታችን ባለው ሳምንት ውስጥ አንደበትህ/ሽ ዝም አይበል።

# ጥናት ሰባት (ሩት 4:13-22)

የጥናት ዓላማ: ሌሎች ሲሳካላቸውና ደስ ሲላቸው ከመቅናት ይልቅ እኛም ከነርሱ ጋራ በመደሰት እግዚአብሔርን መባረክ እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ዛሬ የሚቤዥ የቅርብ የስጋ ዘመድ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ በመላው እስራኤልም ስሙ ይግነን።» ሩት 4:14

1. በቁጥር 13 ላይ በሩት ሕይወት ውስጥ ሲከናወኑ የሚታያቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ዘርዝር።
2. በዚህ ምንባብ ውስጥ ዋነኛ ተዋናኞቹ እነማን ናቸው? ከተዘረዘሩት መካከል በሩት ህይወት በሆነው ነገር ዋነኛ ተደሳች ሆኖ የሚታየው ማን ነው?
3. ይህንን ክፍል ስታነብ ስለሩት ማንነት አካባቢዋ ስላለው አመለካከት ምን ተረዳለህ?
4. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሮሜ 12:15 ትን በተግባር በማሳየት ግልጽ የሚያደርገው ሃሳብ የትኛው ነው?
5. ቦኤዝን የመሰለ ሰው እግዚአብሔር ለሩት ሲሰጣት ጎረቤቶች በደስታ እንደተሞሉ እናነባለን። አንተስ ለሌላው በሚገጥመው መልካም ነገር ምን ያህል ልብህ በደስታ ይሞላል? ከሌላው ጋራ አብሮ ከመደሰት ይልቅ አብሮ ማልቀስ ስለሚቀል በጌታ ፊት ራስህን ለማየት ጊዜ ውሰድ።

ማጠቃለያ ጥያቄዎች

6. የሩት ስም መጽሐፉን የሞላ ሲሆን የዖርፋ ስም ግን ከምዕራፍ አንድ አላለፈም። ለመሆኑ ሩትን ከእህቷ ከዖርፋ የሚለያት ዋነኛ ነገር ምንድነው?
7. በሩት 2:5-7 መሰረት የቦዔዝ ሰራተኞች ስለሩት ሲነግሩት ያተኮሩበት ዋነኛ ሐሳብ ምን ነበረ?
8. በጊዜው ገንዘብ ያላስወጣ ነገር ግን የሩትን ሕይወት ዛሬ ከነበረችበት እንድትደርስ የረዳት የቦኤዝ ስጦታ ምን ነበረ? ሩት 2:8-13 መመልከት ይቻላል። ማንም ሊሰጠው የሚችልና ማንም ሊቀበለው የማይወድ ሰለሌለ ለመስጠት ዝግጁ ሁን።
9. የሩት ትዕግስት የተጠየቀበት ጊዜ የትኛው ጊዜ ነበረ? ለመታገሷስ በቂ ምክንያት ሆኖ ከኑሃሚን የተነገራት ሃሳብ ምን ነበረ? ለኛ ያለውን ትምህርት ተናገር።
10. የመጽሐፉን አጀማመርና አጨራረስ በማነጻጸር ተናገር።